ሰኔ 16 ቀን 2003 ዓ.ም

# ዓሣን ወደ ተራራ፣ ዝንጀሮን ወደ ባህር

ከአያልነሽ

በወያኔ የተገደለው የወያኔ የስለላ ድርጅት ዋና ኃላፊ የነበረው ክንፈ ገ/መድህን፣ በወያኔ ከመገደሉ ከዛሬ 18 ዓመት በፊት፣ ወዲህ ወደ አሜሪካ ብቅ ብሎ ኢትዮጵያዊያንን አነጋግሮ እንደነበር አይዘነጋም። ክንፈ ገ/መድህን ያኔ በመጣበት ወቅት እነኝህን ኢትዮጵያዊያንን ሲያነጋግር ኢትዮጵያን ወደ መቀመቅ ለማውረድ ተዘጋጅተው የመጡበትን ዕቅዳቸውን እንዴት ሥራ ላይ ማዋል እንዳለባቸው፣ ሳይሸሽግ ነበር ያስቀመጠው። መቼስ የለገሠ ዜናዊው ወያኔ ምስግና ይግባውና፣ ከደርግ/ኢሠፓው አገዛዝ የሚለየው ("ለ" ላላ ብላ ትነበብልኝ) በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያለውን ጥላቻ፣ በአደባባይና በአዋጅ እየለፈፈና እያስለፈፈ የመጣ መሆኑ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ እውነታው ይሄንን አዋጁን ደግሞ ተቀብለው ይበል፣ ይበል እያሉ ነፍስ የዘሩለት ሰዎች ዛሬ፣ ዛሬ አንዳንዶቹ በተቃራኒው ቆመናል ብለው **"ነፍሳችንን ሊያጠፋው ነው"** እስከማለትም ደርሰዋል። የሆኖ ሆኖ የወያኔው ወኪል ክንፈ ይህንን ዕቅዱን ለማስረዳት በመጣበት አጋጣሚ ታዲያ አንድ እውነታ ተናግሮ ነበር። ይህ እውነታ ምንድር ነው ? እንዲህ ይነበባል፥

> *አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ የሆነ መንግሥት አገሪቱን ለማስተዳደር በዝግጅት ላይ ነው። ታዲያ ይህንን ጮርቃና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን ዴሞክራሲያዊ ሂደት በአግባቡ እናስኬደው ዘንድ፣ የናንተ የኢትዮጵያኖች ትብብር ያስፈልገናል፤ ሆኖም፣ አለ ክንፈ፣ ሆኖም ይህንን ዕቅዳችንን ተግባራዊ ለማደረግ ትልቁ ደንቃራና እንቅፋት የሚሆነው ደግሞ እንደምታውቁት ኢሕአፓ ነው። ነገር ግን አሁንም ቢሆን ኢሕአፓ ከፈለገ "በሠላማዊ መንገድ" ሊታገል የሚችል መሆኑን እየገለጥን፤ ኢሕአፓን ግን እኛ እስከምናውቀው ድረስ "ጸረ ሠላምና ጦረኛ " ነው። በመሆኑም ይህንን ዕድል አይጠቀምበትም ብሎ ክንፈ ንግግሩን ሲያጠቃልል አስምሮበት ያለፈው አንድ አብይ ጉዳይ ፣ ያም ሆነ ይህ ግን የኢሕአፓን "ግትርነት" ገትረው የሚይዙልን ኃይሎችን ለኢሕአፓ በፀጉሩ ልክ "<u>ድርጅቶች እና ግለሰቦችን እንፈጥርለታለን</u>" ብሎ ነበር።*

ይህን የክንፈ ገ/መድህንን ንግግርና እውነታ፣ ለእኔ ብጤ ጥራዝ ነጠቆች ከያኔ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የለበጣ አነጋገር ሲመስላቸው ቢቆይም፣ ለወያኔ/ህወኃት ግን አንዱ የስጋት ምንጭ እውነትም ኢሕአፓ ነበረና ይህንን የስጋቱን ምንጭ ለማድረቅና ይቋቋመውም ዘንድ፣ **"በተቃዋሚ"** ስም ኢሕአፓን የሚቋቋሙ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ሊያሰልፉ እንዳቀዱ የ20 ዓመቱ የወያኔ ቆይታ አሳይቶናል። ልብ በሉ! ይህ ብቻ አይደለም። ክንፈ ገ/መድህን ያህንን የተናገረውን አባባል የሰሙ የኢሕአፓ አባላት የክንፈ ንግግር ምንጩ የወያኔ ጭንቀት መሆኑን ተረድተዋልና ክንፈን ይበልጥ ለማናገርና ዕቅዱን እንዲያዝረከርክ ለማድረግ፣ በጥያቄ ማጣደፍ ያዙ። ያኔ ታዲያ የክንፈው ወያኔ ሥልጣን ላይ ነኝ ብሎ ያበደበት ወቅት ነበርና **"ኢሕአፓ በሠላማዊ መንገድ መታገል ይችላል"** የሚለውን አባባሉን አጣጥለው የወያኔን ማንነት በአደባባይ ዘረገፉለት። በዚህ የተናደደው ክንፈ ለኢሕአፓ አባላት ማናደጃ ብሎ ነው መሰል በተጨማሪ እንዲህ ሲል ስጋቱን አጋለጠ።

> *ኢሕአዴግ፣ አለ ክንፈ፣ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ተደላድሎ ለመግዛት ኢሕአፓ እስካለ ደረስ አያስችለውምና ይህንን ደንቀራ የሆነ ድርጀት ለመቋቋም፣ ለኢሕአፓ አፍና ፕሮፓጋንዳ መዝጊያ ብቻ የሚያገለግሉ ወይም የሚሰሩ ብዙ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ለመግዛትና ለመፍጠር የሚያወጣውን ገንዘብ በዕብሪት ተናገረ። ለገሠ ዜናዊ አለ፣ ለገሠ ዜናዊም ኢሕአፓ እስካለ ድረስ እንቅልፍ እደማይወስደው አስረግጦ ደነፋ። የሚያሳዝነው ግን ዛሬ ክንፈ እንዲህ በደነፋለት ድርጅቱና አለቃው እጅ ሰለባ ሆኖ ህይወቱ አልፏል።*

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

ይህንን ጉዳይ ያመጡሁት ያለምክንያት አይደለም። ወያኔ ጠላቱን በደንብ ያውቃል፤ በአንፃሩም ጠላቱንም አይንቅም። ይህ ከላይ የተቀመጠው የክንፈ ንግግር አንድም ውሸት የለውም። ዳሩ ግን ዛሬ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ፣ ውሸት እንደ ከበረ ዕንቁ በአደባባይ አሸብርቃና ተሸሞንሙና እኔ ነኝ እያለች መድረክ አልበቃት ብሏልና የውሸት አጀቧ ስለበዛ፣ ለጊዜው ጥግ የያዘችውን ብቸኛዋን እውነት ከተደበቀችበት ታዛ አውጥቸ ፀሐይ አስመታት ዘንድ የክንፈን ሥጋት ይበልጥ የሚያጠናክርልኝን የአለቃውን ንግግር በተጨማሪ ለአብነት እነሆ ላቅርበው! ።

**<u>ፖል ሄንዝ፥</u>** ድርጅታችሁን "**ግንባር**" ብላችሁ ነው የምትጠሩት፣ ግንባር ደግሞ የተለያዩ ድርጅቶችን ያቀፈ ፓርቲ የሚጠቀምበት ስያሜ ነው። ከህወሓት ውጭ ያሉ ድርጅቶች ምንድር ናቸው?

**<u>የሰውየው መልስ፥</u>** እንዲህ ይላል፤ በአሁኑ ጊዜ ሌላ ድርጅት የለም። ትግራይ ውስጥም ስማችን "ሓርነት" ንቅናቄ የሚል ትርጉም ነው ያለው። ወያኔ የሚለውን አጠቃቀም የምንጠቀምበት ምክንያት ትግራይ ውስጥ ታሪካዊ ትርጓሜ ስላለው ነው። (<u>አንባቢዎች ይህን የሚቀጥለውን ዐረፍተ ነገር ላይ ልብ ብላችሁ አንብቡልኝ</u>) ሠረዝ የኔ፣ ትርጉሙ ደግሞ በውጭ ኃይሎች ላይ የሚካሄድ ህዝባዊ አመፅ ማለት ነው። በ1943 ዓ.ም-ም ተመሳሳይ ትግል ተካሂዷል - ትግራይ ውስጥ። ትግሉ፣ ይላል ለገሠ፣ ትግሉ የሸዋን ጭቆናና የበላይነትን የሚቃወም ነው የነበረው።! ደርግም ደግሞ "**ወያኔ**" ብሎ ነው የሚያጣጥለን። እኛ ግን ስያሜውን እንወደዋለን። እና በፖለቲካ ደረጃም የተባበርን ንቅናቄ ነን፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ሃሳቦችና አመለካከቶች እንፈቅዳለን፤ በውሳጣችን በግልፅና በነፃነት የመወያየት ባህል አለ።

**<u>ፖል ሄንዝ</u>፥** ኢሕዴን ይህ ነው የሚባል ነፃነት የለውም። በራሱ መቆም የሚችልም አይደለም የሚባል ነገር ሰምቻለሁ፤ ... ሰዎች ሕወሓት ጠፍጥፎ የፈጠረው ድርጅት እንደሆነ ነው የሚናገሩት። እውነት ነው?

**<u>ለገሠ</u>፥** ኢሕዴን እንደህወሓት በደንብ የተደራጀ ንቅናቄ ነው ባይባልም፣ እኛ ጠፍጥፈን የፈጠርነው ደርጅት ግን አይደለም። በደቡብ ትግራይ የሚኖሩ ጭቁን አማራዎችን የሚወክልና የነዚህን ጭቁኖች ተስፋ የሰነቀ ነቅናቄ ነው። ዋና ጽ/ቤቱም በሰቆጣ ይገኛል።

**<u>ፖል ሄንዝ</u>፥** ከኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (**ኢሕአፓ**) ጋር ያላችሁ ግንኙነትስ ምን ይመስላል?

**<u>ለገሠ</u>፥** ከኢሕአፓ ጋር ያለን ግንኙነት መልካም የሚባል አይደለም። ድርጅቱ በአብዮቱ ማግሥት ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ እንደነበር እሙን ነው። ነገር ግን በቀይ ሽበር ወቅት ብዙ ጉዳት ደርሶበታል (ቂ ቂ ቂ ቂ የአዛኝ ቅቤ አንጓች ይሏል እንዲህ ነው።) ከዚያ በኋላ ጥንካሬያቸውን ጠብቀው መቀጠል አልቻሉም። እነርሱ ማለት ይላል ለገሠ፣ እነርሱ ማለት የደርግ ሌላኛው ገፅታ ማለት ናቸው። የአማራ የበላይነትን ይደግፋሉ።... ማርክሲስቶች ናቸው። አቋማቸው የኢትዮጵያዊያንን እኩልነት ይፃረራል። አመለካከታቸውን እስካልቀየሩ ደረስ ከነርሱ ጋር ትብብር መፍጠር ያስቸግረናል። ህዝቡም ይደግፋቸዋል ብዬ አላስብም ወዘተ...ይልና መለስ በዚሁ ከፖልሄንዝ ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ቆይታው ከመኢሶን ጋርስ ተብሎ ለተጠየቀውም "**ከመኢሶን ጋር ...ለመስማማት አንቸገርም**" ከኦነግ ጋርም "**...በቀላሉ መተባበር የምንችል ይመስለኛል**" ሲል እቅጩን ተናግሮ ነበር።

ወያኔ በኢሕአፓ ላይ የማያወላዳና ጥርት ያለ አቋም እንዳለው፣ ከዚህ በላይ ምንም ማረጋገጫ ማግኘት አይቻልም። ከንፈም ሆነ የወያኔው አለቃ ለገሠ ዜናዊ፣ በኢሕአፓ ላይ ይሄን መሰል አቋም ሲይዙ፣ ትናንትና ምኒልክ ቤተ መንግሥት የገቡ ዕለት ሳይሆን፣ ገና ከጥንት ከጥዋቱ ወያኔ እንደ ድርጅት ዳዴ ማለት ባልጀመረበት ወቅት እንደነበር የኢሕአፓንና የወያኔን የትግል ታሪክ የሚያውቅ ሁሉ ሊስተው አይችልም። የኢሕአፓና የወያኔ ልዩነትና ቅራኔ ደግሞ እንደስማቸው ሁሉ መሠረታዊ፣ እንዲሁም የማይታረቅና ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ እንዳላቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከወያኔ በላይ የሚያውቅ የለም። ታዲያ ይህ ሆኖ እያለ እውነታው፣ ከትናንት ጅምሮ እስከዛሬ ደረስ በየአቅጣጫው ተንሥተው ከጳጳሱ ቄሱ እንዲሉ ከወያኔ በላይ ሆነው ወያኔን በሚያስከነዳ መንገድ ኢሕአፓን ዓይንህን ለአፈር እያሉ 24 ሠአት ሙሉ ሲራገሙና፣ ወገባቸውን በመስበቅ ያዙን ለቀቁን የሚሉተን ለተመለከተ ፣ ይህ ሁሉ ግብግብ ምናልባትም ከንፈ እንዳለው የወያኔው ዕቅድ ምን ያህል ተግባራዊ እየሆነ እንደሆነ አመላካች ነው።

እዚህ ላይ ግን አንድ ሐቅ አለ። ወያኔ **የኢሕአፓን** ስም በጭራሽ አያነሳም - ለዚህም ምክንያት አለው። ለገሠ ዜናዊ የኢሕአፓን ስም ላለማንሳት መሐላ የገባባት ዋናው ምክንያት ደግሞ፣ የባሕረ ነጋሹ መጽሐፍ ፀሐፊ እንደሚለው ኢሕአፓን ንቆ ሳይሆን፣ የኢሕአፓን ስም በመጥፎም ሆነ በጥሩ ማንሳት፣ ምንጊዜም ቢሆን ወያኔ የቆመበትን የመንደርተኘነት መሠረት የሚያናጋበትና የሚንድበት ስለሆነ ብቻ ነው። ለዚህም ነው ወያኔ ከኢሕአፓ ጋር የሚያደርገውን የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ሁሉ በወኪል (በ-Proxy) ማድረግን የመረጠው። ለነገሩማ ደርግ/ኢሠፓም እኮ እስከ መጨረሻው የመውደቂያ ሰዓቱ ድረስ፣ የኢሕአፓን ስም እርም ብሎ ሳያነሳ ቆይቶ ነው ወደ መቃብሩ የወረደው። ለዚህ ደግሞ ማስረጃው፣ መውድቂያው ደረስ አብረው የቆዩትና የከረሙት

በስተመጨረሻም አብዮታዊ መሪያቸው "**ሂሳዊ ክኒኑን**" እንዲወስድ ሲማፀኑ የነበሩት መስከረምተኞች የዓይን ምስክሮች ናቸው።

የተከበራችሁ አንባቢዎች!

አስታውሱ! በ1983 ዓ.ም ግንቦት ላይ ወያኔ አዲስ አበባን ሲረግጥ አዲስ የተራበ ወንበዴ ነበርና፣ ወደ አዲስ አበባ አገባቡንና ቆይታውን ፣ እንደ ሳህል በረሃ ቆይታው አቅልሎ ያየው እንዳልነበር ብዙ ያልወጡ መረጃዎች ያመላከታሉ። ለምን ብሎ የሚጠይቅ ካለ መልሱ ግልፅና አጭር ነው። ለወያኔ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና መዲና መሆኗ ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያ ራሷ ትልቅ አገር መሆኗን የተረዳው እዚያ ሲደርስ ለመሆኑ ዋቢ መጥቀስ አያስፈልገም። ታዲያ ይህ የተራበ አዲስ ጅብ አገር ያላምዱት ዘንድ ከየቦታው ቃርሞ ያመጣቸውን ግለሰቦች በድርጅት ስምም ሆነ በግለሰብ አግተልትሎ ጭንብል በማልበስ፣ ኢሕአዴግ ነኝ በማለት "**የምኒልክ ሐውልት ይፍረስ**" እስኪሉ ጮቤ አስረገጧቸዋል።

ወያኔ/ህወሓት-ኦች ግን አዎ ነገር ዓለሙን ሁሉ አዛብተው ማቅረብ ዕድገታቸውና ባህሪያቸው ነውና ዛሬ ዛሬ የሚፎከሩለት ጀግነነት ያልተፈተነ ይመስል "**ተዋግተን ገባን**" እያሉ እንደሚያወሩትና እንደሚያስወሩት እንዳልሆነ የአዲስ አበባ ሕዝብ ያውቃል። ዳሩ ግን ለገሠ ዜናዊ ዛሬን የሚያሳድረው ከሆነ፣ ውሸትና ቅጠፈት ሃብቱ ነውና፣ ለጋዳፊም ቀድሞ "**አረብ**" ነን ብሎ እግሩ ሥር ሲደፋ ጊዜ ያልወሰደበት፣ በዚሁ በተጣባው ቅጥፈቱ ለመሆኑ አገር ያውቀው ጉዳይ ነው። ግን የለገሠ ዜናዊ ቅጥፈትና ውሸቱ ይግባናል። በአንድ ፊቱ ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የሚጠቀምበት ፈርንጆቹ "**ነጭ ውሸት**" የሚሉት በመሆኑ ዓለም ሁሉ ተረድቶት በተደመመበት ሁኔታ፣ የእሱ "**ተቃውሚ**" ነን የሚሉ ኃይሎች ግን ከመለስ ዜናዊ ውሸት በልጠው በሠዓታት ልዩነት የውሸት ክምር ሲያመርቱና የከመሩትንም የውሸት ዝግንተል መሰብሰብ እስኪቸግራቸው ድረስ የሚሄዱትን ምን እንበላቸው? የሚገርመው ለእንዲህ ዓይነት ውሸታቸው ደግሞ እስዬ አበጃችሁ በማለት አንገታችንን እንሰጣለን ለሚሉ ስዎችቻቸውስ ምን ብለን እንሠይማቸው?

ኢሕአፓና ወያኔ በደንብ ይተዋወቃሉ። ትውውቃቸው ደግሞ የፍቅር ሳይሆን የባላጣነት መሆኑ የትግል ገድላቸው ያስረዳል። ባላንጣነታቸው ደግሞ በሌላ ሳይሆን በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ በሕዝባችን የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የመሆን ጉዳይ ላይ ያጠነጠነ ነው። ኢሕአፓ ጊዜውን፣ ጉልበቱን፣ ገንዘቡን ያለ የሌለ የሰው ኃይሉን ሁሉ የሚያጠፋውና የሚጠቀመው በእርግጥም የወያኔን ውደቀት በቶሎ ለማፋጠንና የሚመኘውን የሕዝብ የባላይነት ደግሞ ለማቃረብ ስለሆነ ይህንን ተግባሩን ዳርቻው ድረስ ለማደርስ የሚሠራ ለመሆኑ፣ ከወያኔ የተደበቀ አይደለም። ወያኔም የኢሕአፓ ነገር የሚጠዘጥዘውና ከብብቱ ሥር እንዳለ ጠንቅቆ ያውቀዋል። በዚህ ደግሞ በጣም ተደሳቹ ኢሕአፓ ነው። ይሄ ታዲያ ለምን ሌሎችን ያበሳጫል...ቅ ቅ ቅ ቅ ? በውነቱ ኢሕአፓ በወያኔ ላይ ማከረሩስ ሲያንስ እንጅ ይበዛበታልን? እንዲያው ለነገሩ ኢሕአፓ ወያኔን "**ኢሕአዴግዬ**" እያለ ሲያወደስ ቢገኝ እንጅ የሚያስደነቅው፣ "**አክራሪነቱማ**" ከቶ ለምን ይሆን ሌሎችን እንቅልፍ ነሥቶ ኢሕአፓን "**በኋላ ቀር፣ በፋራ ፖለቲከኛነትስ**" ያአስፈረጀው? ጎበዝ! ይሄ ነገር የጤና ነው ትላላችሁ?

በነገራችን ላይ አንዳንዶችማ በኢትዮጵያ ምደር ለተፈጠረው ችግር ሁሉ ተጠያቂው " **አክራሪው የግራ ፖለቲከኛ ኢሕአፓ ነው**" እስከማለት ይደረሱና፣ የኢትዮጵያን ታሪክ ለእኛ ለመሃይሞች ሊያስተምሩ ታሪክ ሲያጣቅሱ ደግሞ፣ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጅምሮ እጅግ ወደኋላ ርቀው በመመለስ፣ ኢሕአፓ የተባለው "**እርጉም**" ባልተፈጠረበት ዘመን ሁሉ የነበረ ጣጣን እየዘረዘሩ፤ ኢሕአፓ ኢትዮጵያዊነቱ እስኪሠረዝ ድረስ ይወግሩታል፣ ይወቅሩታል - አጀብ! ግን ለምን ? ደግነቱ ላይችል አይሰጥ ይባላልና፣ ኢሕአፓ ከተፈጠረ ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ፣ ምን ያልተባለው ነገረ አለና ነው ዛሬ ይህንን አዲስ አስመሰለው አንበሳ ገዳይ የሚያሰኛቸው። ኢሕአፓ እኮ "**ከአናርኪስት እስከ ዓባይ ኢትዮጵያ፣ ከትምክሕተኛ እስከ ማርክሲስት ሞገደኛ፣ ከጦረኛ እስከ አክራሪ ፋራ ፖለቲካኛ** የቀረ ነገር አለ? ወዘተ... ምን ያልትባለው አለና ነው።
መቸ በዚህ ብቻ ቆሞና የኢሕአፓ እርግማን? ገፋ ሲለም በምስራቁም፣ በምእራቡም በሱዳንም ሳይቀር፣ በአሽከሮቻቸው አማካኝነት በኢሕአፓ ላይ ያ ሁሉ ጦር ተሰብቆበት አልጠፋ ያለ ደርጅት ለመሆኑ እንኳንስ ወድጃ ቀርቶ የምር ባላንጣዎቹ እንኳ አይክዱትም። ያንን ሁሉ ያሳለፈ ደርጅት ነውና የዛሬው የግራ ፖለቲካኛ ነው ለቅሶና ዋይዋይታ፣ ለኢሕአፓ የሚያስበረግገውና አዲሱ አይደለም። ይልቁንስ ዛሬ ኦባማም በጤና ኢንሹራንስ ፖሊሲው (Health care) ምክንያት "**ያበደ ኮሚኒስት**" እየተባለ ነውና እኩል ለእኩል ሆነናል እያልኩ Welcome to EPRP በማለት ብራቮ ኦባማ - ቸርስስስስስስ ብዬ ቡናዬን አጋጭቻለሁ ሃ ሃ ሃ ሃ!

## የሕዝብ ትግል ያቸንፋል! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ይገጠመን!
june 23/ 2011